## በአፄዎና በልፈፋ ደረጃማ ቢሆን...
## ንጉሡም፣ ደርግም ወያኔም ሰብዓዊ መብት አክባሪያቸ ነበሩ

ዛሬ የወያኔ መንግሥት ከየአገጣጫው የሰው ልጅ መብት ይረገጣል እየተባለ ነጋ ጠባ
የሚወገዝ ስመ ጥፉ መንግሥት ነው:: በዓለም ላይ የሰው ልጅ መብት ይረገጣሉ የሚባሉ መን
ግሥታት ብዙ ቢኖሩም እንደዚህ ላላሰለሰ ውግዘት የሚዳረጉ መንግሥታት በጣት የሚቆጠሩ ናቸ
ው:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት ለምንድን ነው ቢባል ሶስት ዋና ዋና ነጥቦቸ ይታዩናል::

የመጀመሪያው ምክንያት በመካሄድ ላይ ያለው የመብት ረገጣ እጅግ የሰፋ፣ ምንም ገ
ደብ የሌለውና በተሄደበት አገጣጫ ቢኬድ ይህንን መንግሥት አሳፋሪ ከብረ ወሰን የሚያስይዝ
ረገጣ መሆኑ ነው:: በኢትዮጵያ በፖለቲካ ምክንያት ከ10ሺ ዜጎቸ በላይ በእስር ቤት ይገ
ኛሉ:: በቀረው አፍሪካ ያሉ የፖለቲካ እስረኞቸ ቢደመሩ ይህንን አያክሉም:: ባለፈው ሳም
ንት አምኒስቲ ኢንተርናሽናል የሰብዓዊ መብቶቸ ዓለም አቀፍ አዋጅን 50ና ዓመት ክብረበዓ
ል አስመልክቶ ባወጣው ሪፖርት ህዳር ወር አጋማሽ ላይ በመላ ዓለም በእስር ላይ የሚገኙ
ጋዜጠኞቸ ቁጥር 92 መሆኑን ገልጾ ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚገኙት በአራት ስመ ጥፉ
አገሮቸ እንደሆነ አስታውቋል:: እነሱም አንደኛ ኢትዮጵያ 15 ጋዜጠኞቸ፣ ሁለተኛ ቻይና
14 ጋዜጠኞቸ ሶስተኛ ሲርያ 10 ጋዜጠኞቸ፣ አራተኛ በርማ ሰባት ጋዜጠኞቸ ናቸው::በአፍ
ሪካ ጋዜጠኞቸ የታሰሩባቸው አገሮቸ በድምሩ 11 ሲሆኑ በጠቅላላው በእስር ላይ ~~የ~~ሚገኙት
~~ጨጨጨ~~ 29 ጋዜጠኞቸ ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ሁለተኛው ~~ሙሙሙ~~ በሰው ልጅ መብት ጉዳይ የወያኔን መንግሥት እንደጉድ እንዲታይ ያ
ደረገው ነገር በዛሬይቱ ዓለም በመንፈስ ላይ ካለው የዲሞክራሲ ንፋስ ጨርሶ የሚጻረር ሂደ
ት በመያዙ ነው:: ዛሬ ሌላውን ተተን በአፍሪካ እንኳን ያለውን ሁኔታ ብንመለከት ከእለ
ት እለት ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ አገሮቸ ዲሞክራሲን እየተላበሱ ሲሄዱ እናያለን::ከደ
ቡብ አፍሪካ እስከቤኒን፣ ከማዳጋስካር እስከጋና ድረስ የሰው ልጅ መብት ከእለት እለት እ
የተረጋገጠ፣ በነጻና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መንግሥታት እየተፈራረቁ አገር የሚያስተዳድሩበት
ወቀት እየገባን ነው:: ከዚህ አፍሪካን ከማዳረስ ላይ ካለው ሂደት ኢትዮጵያን ነጥለ
ው በማስቀረታቸው የወያኔ መሪያቸ በብዙ አፍሪካውያን፣ እጅግ የተናቁ፣ በብዙ ዓለም አቀፍ
ታዛቢያቸ ዘንድ ደግሞ እጅግ ኋላ ቀርና አሽቀብ ለመፍሰስ እንደሚገደረደር ውሃ ~~አ...~~ቸ
~~ቀ...~~ ኋላቀርፕሬቸዋል። “ፋኖን የመሳለች አገር እንደዚህ አደረጓት” በሚሉ:

ሶስተኛው ወያኔን እንደጉድ እንዲታይ ያደረገው ምክንያት ቢያንስ በልፈፋ ደረጃ በ
ሰብዓዊ መብት ~~ጨጨ~~ መከበር እምናለሁ፣ ዓለም አቀፉን የሰብዓዊ መብቶቸ አዋጅ በይፋ ተቀብ
ያለሁ ማለቱና የሚሠራው ሁሉ ከዚህ ጋር በየእለቱ ሲጋጭ መታየቱ ነው:: የወያኔ ደጋፊያቸ
ና አንዳንድ ባእዳን አጋሮቻቸው እንዲያውም እንደዋና መከራከሪያ አርገው የሚያቀርቡልን ይ
ህንኑ ነው::“የዛሬው መንግሥት ቢያንስ ቢያንስ ሰብአዊ መብቶቸን በይፋ ተቀብሏል፣ እነዚ
ህን መብቶቸ በዝርዝር በህገመንግሥቱ ላይ አስፍሯል፣ ይህ ትልቅ ርምጃ ነው፣ ከእንግዲህ
የሚቀረው ቀስ በቀስ ተግባራዊ የመሆናቸው ጉዳይ ብቻ ነው” የሚሉትን ነጥቦቸ ነው:: ነገር
ግን ይኸ የሚያዋጣ መከራከሪያ አይደለም::

በያዝነው ክፍለዘመን በህዝባቸን ትከሻ ላይ ሶስት አስከፊ ሥርዓቶቸ ተፈራርቀውበታ
ል:: በልፈፋና በአዋጅ በመቀበል ደረጃ ከሆነ ሶስቱም በየወቅቱ ከውጭ አሳዳሪያቻቸው በቀ
ለቧቸው መፈክሮቸ እየተመጻደቁ ሰብአዊ መብቶቸን በይፋ ያወጁልን አገዛዞቸ ነበሩ:: የአጼ
ኃይለሥላሴ መንግሥት “በዘመኑ ሥልጣኔ” ስም:: የደርግ መንግሥት “በሶሻሊዝም ግንባታ” ስም::
የወያኔ መንግሥት ደግሞ “በመድበለ ፖርቲ ሥርዓት” ስም:: በመታወጁና በልፈፋ ደረጃ ቢለካ
ኖር ቢያንስ ቢያንስ ከ1948ዓ.ም. የተሻሻለው ህገ መንግሥት ጀምሮ ሃገራቸን የሰው ልጅ
መብቶቸ ሙሉ በሙሉ የተረገጡባት ሳይሆን የተረጋገጡባት ሃገር በሆነቸ ነበር:: ነገር ግን

ሰስቱም አገዛዞች እነዚህን መብቶች ለፈፉልን እንኳ የእነዚህን መብቶች መከበር ለማረጋገጥ ራሳቸው ከህግ በታች ሆነው የሚተዳደሩበት ህገ መንግሥት ስላልነበራቸው ዋስትና ባለው ሁኔታ መብቶቹ በተግባር የሚውሉበት ተዓምር አልነበረም:: ይህንን የዋስትና ጉዳይ እያድበሰበሱ እስካለፉ ድረስ ደግሞ የፈለጉትን ያህል መብት ቢደረድሩልን ምንም የሚያስጋቸው ነገር ባለመኖሩ የአጼ ኃይለ ሥላሴም፣ የኩለኔል መንግሥቱም የአቶ መለስ ዜናዊም መንግሥታት በዚህ በመብት ማወቅ ጉዳይ እንደልብ ሲፈልሉ ታዝበናል:: የመጀመሪያና የመሠረታዊ፡ መብቶች

የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት የ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ህገ መንግሥት ሰብዓዊ መብቶችን በ28 አንቀጾች የዘረዘረና አውቆያለሁ ያለ ህገ መንግሥት ነበር:: የኘሬስ ነጻነት፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት ምብቶች ... ያልታወቀ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት አልነበረም:: ንጉሡ እንዲያውም የተሻሻለውን ህገ መንግሥት ለወቀቱ ፓርላማ ሲያቀርቡ ጥቅምት 23 ቀን 1948 ዓ.ም. ባደረጉት ንግግር ህገ መንግሥቱ 'ሰብዓዊ መብቶችን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ከሰለጠኑት ሃገሮች የተወሰዱ አንቀጾችን' የያዘ መሆኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ አበሰረው ነበር:: ደርግም በበኩሉ እነዚህን መብቶች በ24 አንቀጾችና በ56 ንኡስ አንቀጾች ቃል ገብቶልን ነበር:: ወያኔ በ30 አንቀጾችና በ103 ንኡስ አንቀጾች ከደረደረልን በኋላ ካለበቃቸሁ ብሉ ዛሬ አምሳና ዓመቱን የምናከብረውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት አዋጅ አከሉልናል::

ታዲያ ለኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህ ሁሉ መብቶች ታውቀውለታል እየተባለ ለምን በሰስቱም አገዛዞች የመብት ጉስቋላ ህዝብ ለመሆን በቃ?

የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለህዝቡ አወቀሁ የሚላቸውን መብቶች በሙሉ በዚያው በህገ መንግሥቱ ውስጥ 'በህጉ መሠረት' በሚል አንቀጽ ይቀላልፋቸው ነበር:: የደርግ ህገ መንግሥት ደግሞ በአንቀጽ 58 በሰነዱ የታወቁት መብቶች 'የመንግሥትንና የህብረተሰቡን ጥቅም ለማስከበር" ሲባል ሊታገዱ እንደሚችሉ ይደነግጋል:: የኢህአዴግም መንግሥት እንደዚሁ በተለያዩ አንቀጾች ሊታገዱ እንደሚችሉ ይደነግጋል:: ለምሳሌ የግል ህይወትን የመከበርንና የመጠበቅን የመሰለ መሠረታዊ መብት ቢያውቅም ይህ በአንቀጽ 26/3 የታወቀ መብት አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትንና የህዝብ ሰላምንና ወንጀልን ለመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት ለማረጋገጥ ሲባል አጠቃቀሙ ሊገደብ እንደሚችል ይደነግጋል::

ችግሩ እነዚህ በህግ መሠረት የሚደረጉ ገደቦች መኖራቸው አይደለም:: ችግሩ የዳኝነት ነጻነትና የህገመንግሥት ቁጥጥር በሌለበትና ገዥዎች ከህግ በላይ በሆኑበት ህብረተሰብ ውስጥ ህዝቡ በእነዚህ መብቶች ሲጠቀም በህጉ መሠረት መሆኑን አለመሆኑን፣ የህብረተሰብን ጥቅም መጻረሩን አለመጻረሩን፣ የሃገር ደህንነት ማናጋቱን አለማናጋቱን፣ ለህዝብ ሞራል አደገኛ መሆኑን አለመሆኑን...ባጭሩ እነዚህ መብቶች መገደብ አለባቸው የለባቸውም የሚለውን ጥያቄ የሚወስኑት ራሳቸው ገዥዎቹ መሆናቸው ነው::

የሃገራችን ችግር በጠቅላላው በህብረተሰቡ ዲሞክራሲ መነፈግ ጋር ተያይዞ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ዳኝነት የሚሰጥም ሆነ ህገ መንግሥቱን የሚተረጉምና ባለሥልጣኖችም በህጉ መሠረት መሥራት አለመሥራታቸውን የሚቆጣጠር ነጻ አካል አለመኖሩ ነው:: የወያኔ ህገ መንግሥት እንደ አጼ ኃይለሥላሴና እንደደርግ ህገ መንግሥቶች በዚህ መልክ የህግ የበላይነትን የሚቆጣጠርና የሚያረጋግጥ ነጻ አካል ስለሌለው በዚህ ሁኔታ ሰብአዊ መብቶች ይከበራሉ ማለት ዘበት ነው::